# ወርሃዊ የአየር ጠባይ

# ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## ከኦገስት 1-31/2021 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ እንዲሁም

## ከሴፕቴምበር 1-30/2021 የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ሴፕቴምበር 2021
አዲስ አበባ

ርዕስ ገፅ


እ.ኤ.አ ከኦገስት1 እስከ 31/2021 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ ....2

ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ....3

ካርታ 7 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2021 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት ....4

ካርታ 8 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ....5

እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2021 የነበረው የአየር ጠባይ በእርሻ ....6

ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ....6

ካርታ 9 ከኦገስት 1 እስከ 31/2021 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ....6

እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2021 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ....7

ካርታ 10 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2021 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ....7

እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2021 የሚኖረው ....8

የአየር ጠባይ አዝማሚያ ....8

እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2021 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....9

እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2021 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሀው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....10

## እ.ኤ.አ ከኦገስት1 እስከ 31/2021 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ


ባለፈዉ የኦገስት ወር የክረምቱ ዝናብ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከሞላ ጎደል ያልተስተካከለ ሲሆን፤ በተለይም በሶስተኛዉ አስር ቀናት አንፃራዊ በሆነ መልኩ ወደ ሀገራችን እየገባ የነበረዉ እርጥበት አዘል አየር ይበልጥ በመዳከሙ በየጣልቃዉ ጸሃያማ ሁኔታ ተዘውተሯል፡፡ በመሆኑም የኦገስት ወር ዝናብ በመደበኛ ሁኔታ ከሚጠበቀዉ በመጠን ረገድ ቀንሶ ተስተዉሏል፡፡

በአጠቃላይ ባለፈዉ የኦገስት ወር በአማራ፣ በምዕራብና መካከለኛዉ ኦሮሚያ፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ በጋምቤላ፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ በሲዳማ፣ በደቡብ ደጋማ ስፍራዎች፣ በአፋር፣ በሰሜን ሱማሌ፣ በሐረሪና ድሬዳዋ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከባድ ዝናብ ከተመዘገበባቸዉ ጣቢያዎች መካከል አንዳንዶቹን ለመጥቀስ ያህል በሻሁራ 35.9፣ 67.6፣ በአይከል 55.0ና 52.2፣ በአምባ ማሪያም 103.5ና 46.0፣ በጭፍራ 33.7፣ በላሬ 36.0፣ በሐረማያ 39.4፣ 43.6፣ በአዲስ አበባ ቦሌ 33.0፣ በአቦቦ 50.2፣ 55.2ና 42.2፣ በደብረ ብርሀን 36.2 እና 53.2፣ በደብረ ማርቆስ 39.2፣ በጋምቤላ 33.2 እና 45.8፣ በማንኩሽ 58.0፣ በማሻ 30.8 እና 46.6፣ በሞጣ 33.3፣ በንፋስ መውጪያ 37.9፣ በአዳማ 69.1 እና 39.3፣ በሰመራ 36.0፣ በኤሊያ 34.2 እና 30.9 በሚሜ. ይገኙበታል፡፡


ባለፈው የኦገስት ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በሁሉም የአማራ፣ በአፋር ክልል ዞን 05፣ 03ና 01፣ የቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ የጋምቤላ፣ በአርሲና ጥቂት የባሌ፣ የወለጋ፣ የኢሉባቦር፣ የጅማ እና የሸዋ ዞኖች፣ በፋፈን፣ ከጥቂት የደቡብ ኦሞ በስተቀር በተቀሩት የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች እንዲሁም በሲዳማ ክልል ዞኖች ላይ ከ100-430 ሚሜ. የሚደርስ ከ10-29 ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፤ በምስራቅና ምዕራብ ሀረርጌ፣ በአብዛኛዎቹ የባሌ፣ የአፋር ክልል ዞን 02ና 04፣ የደገሃቡር እና የጥቂት የጋምቤላ ክልል ዞኖች ላይ ከ25-100 ሚሜ. የሚደርስ ከ10 ላነሱ ቀናት ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 6 እና 7) ፡፡

ባለፈው የኦገስት ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በሰሜን ጎንደር፣ በጥቂት የሰሜን ወሎ፣ የአፋር ክልል ዞን 03፣ የጋምቤላ ክልል ዞኖች፣ በኢሉባር፣ በጅማና ምዕራብ ሸዋ እንዲሁም በፋፈን ዞኖች ላይ መደበኛ ዝናብ ነበራቸዉ፡፡ የተቀሩት አብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ከመደበኛ በታች የሆነ የዝናብ መጠን ነበራቸው (ካርታ 8) ፡፡


ካርታ 6 ኢ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 7 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2021 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት




ካርታ 8 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



# እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2021 የነበረው የአየር ጠባይ በእርሻ ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፈው የኦገስት ወር ለወቅቱ ዝናብ መኖር አመቺ የሆኑት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ከመጠናከራቸው ጋር ተያይዞ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚና የመኸር ሰብል አብቃይ በሆኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ በመጠንም ሆነ በሥርጭት ረገድ ጥሩ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸዉ፡፡ ይህም ሁኔታ የአፈርን እርጥበት ከማሻሻል እንዲሁም ተክሎች የሚያስፈልጋቸውን ውኃ ከማቅረብ አንጻር ገንቢ ሚና ነበረው፡፡ በተጨማሪም ከሰብል ልማት አንጻርም ቀደም ሲል በሚያዝያና ግንቦት ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚኙት የረጅም ጊዜ ሰብሎች እንደ ማሽላና በቆሎ ለመሳሰሉት እንዲሁም በክረምት ወቅት ተዘርተው በቡቃያና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ላሉት እንደ ስንዴ፣ ገብስ፣ አጃ እና ጤፍ ለመሳሰሉት የብርዕ ሰብሎች፣ የጥራጥሬ እህሎችና የቅባት እህሎች እንዲሁም ለቋሚ ተክሎች የዉሃ ፍላጎት መሟላት ምቹ ሁኔታን ከመፍጠሩም በተጨማሪም ለአርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደሩ አካባቢዎች ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሳር አቅርቦት መሟላት በጎ ጎን ነበረው፡፡ በተጨማሪም በተከታታይ ዝናብ በማግኘት ላይ በነበሩ በአንዳንድ የአገሪቱ አካባቢዎች ላይ በተለይም በአማራ፣ በምዕራብና መካከለኛዉ ኦሮሚያ፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ በጋምቤላ፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ በሲዳማ፣ በደቡብ ደጋማ ስፍራዎች፣ በአፋር፣ በሰሜን ሱማሌ፣ በሐረሪና ድሬዳዋ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ የነበረ ሲሆን፤ በዚህም ምክንያት አልፎ አልፎ የመሬት መንሸራተት፤ በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ባሉ ሰብሎች የአፈር ውስጥ እርጥበት መብዛትና ቅጽበታዊ ጎርፍ በተወሰኑ ቦታዎች በመከሰቱ በተለያየ የእድገት ደረጃዎች ላይ ባሉ ሰብሎች፣ በአፈር ጥበቃ ሥራ እንዲሁም በሰው እና በንብረት ላይ መጠነኛ ጉዳት ነበረው፡፡ በአንጻሩ የተሰበሰቡ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት የነበረው ከባድ ዝናብ በአንዳንድ የሰሜን ምዕራብ፤ በመካከለኛዉና በምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ማሳ ላይ ዉሃ መተኛት፤ የመሬት መንሸራተትና ወንዞች መሙላት በመከሰቱ በሰብሎች፤ በሰዎች እና በእንስሳት እንዲሁም በንብረት ላይ መጠነኛ ጉዳት አድርሷል፡፡ በአጠቃላይ በዚህ ወር የተገኘው እርጥበት ቀደም ባሉት ጊዜ የእርጥበት እጥረት ለነበረባቸው ቆላማ የአገሪቱ አካባቢዎች ላይ ለሚኖሩት አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደሩ አካባቢዎች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት ጥሩ አስተዋፅኦ ነበረው (ካርታ 9)፡፡


ካርታ 9 ከኦገስት 1 እስከ 31/2021 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2021 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ከኦገስት 1-31/2021 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ በተመለከተ የተሻለ የእርጥበት መጠን በሀገሪቱ ምዕራባዊ፣ በሰሜን ምዕራባዊ እና መካከለኛዉ ተፋሰሶች ላይ ከበጣም ከፍተኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት መጠን አግኝተዋል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ አብዛኛው አባይ፣ ባሮአኮቦ፣ ተከዜ፣ ኦሞጊቤ፣ የመካከለኛውና የላይኛው አዋሽ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ የላይኛው ዋቢሸበሌ እንዲሁም የላይኛው አፋር ደናከል ተፋሰሶች የተሻለ እርጥበት የተስተዋለባቸው ናቸው፡፡ መካከለኛው ዋቢሸበሌ፣ ገናሌዳዋ፣ ጥቂት የላይኛው አፋር ደናከል፣ የታችኛው አዋሽ፣ የመካከለኛውና የታችኛው ስምጥ ሸለቆ እንዲሁም ጥቂት የታችኛው ባሮአኮቦ ተፋሰሶች መጠነኛ እርጥበት አግኝተዋል፡፡ በመሆኑም በአለፈዉ ኦገስት ወር የተገኘው እርጥበት ለውሃ ሃብት ከፍተኛ ግብዓት ከመሆኑም በላይ በመጠን ረገድ በአንዳንድ ተፋሰሶች ላይ በተከታታይ ከባድ ዝናብ በመኖሩ የወንዞች እና የውሃ ማጠራቀሚዎች ከመደበኛው ወቅት ቀደም ብሎ የውሃ ሙላት ተከስቷል (ካርታ 10) ።

ካርታ 10 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2021 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2021 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ ሴፕቴምበር የክረምት ወቅት የመጨረሻ ወር ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የወቅቱ ዝናብ በብዙ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እየተዳከመና እየቀነሰ የሚሄድ ሲሆን፣ በአንጻሩ ለረጅም ጊዜ ደረቅ ሆነው የሰነበቱት የደቡብና የደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸውን ማግኘት ይጀምራሉ፡፡ የወቅቱ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከሴፕቴምበር በመጀመሪያው አሥር ቀናት ጀምሮ ከሰሜን ምሥራቅና ከሰሜን ኢትዮጵያ እየለቀቁ በመሄድ በምዕራብ፤ በደቡብ ምዕራብና በመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ይወሰናሉ፡፡ በወሩ መጨረሻ ሳምንት ደግሞ የሰሜን ምሥራቅ፤ የምሥራቅና የመካከለኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች በበጋው ደረቅ የአየር ጠባይ ሥር መሆን ይጀምራሉ፡፡

በመጪው የሴፕቴምበር ወር በፀሐይ ሀይል ታግዘው ከሚፈጠሩ የደመና ክምችቶች በአንዳንድ የሰሜን ምዕራብ፣ የምዕራብና የመካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ነጎድጓድ እና በረዶ የቀላቀለ ከባድ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተጨማሪም የክረምቱ ዝናብ ከሞላ ጎደል ከመደበኛዉ ጋር ተቀራራቢ በሆነ ጊዜ ከአብዛኛዎቹ የወቅቱ ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ ሊያቆም እንደሚችል ይጠበቃል፡፡

በአጠቃላይ ሁሉም <u>የትግራይ ዞኖች፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ፤ የጋምቤላ ክልል፤ ከአማራ ክልል ምዕራብ እና ምሥራቅ ጎጃም፣ ሰሜን ሸዋ፣ የዋግሕምራ፣ የባህር ዳር ዙሪያ፣ አዊ ዞን፣ የሰሜንና የደቡብ ጎንደር ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ዞን 5፤ ከኦሮሚያ ክልል ሁሉም የወለጋና የሸዋ ዞኖች፣ ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ የአርሲ ዞኖች፤ አዲስ አበባ፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደግሞ የሀድያና የጉራጌ ዞኖች፣ የወላይታ፣ የዳውሮ፣ የጋሞና ጎፋ፣ የከፋና የቤንች ማጂ፤ እንዲሁም የሲዳማ ዞኖች በአብዛኛው መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከባድ ዝናብ ሊከሰት ይችላል፡፡ በተጨማሪም ምዕራብና ምሥራቅ ሐረርጌ ከኦሮሚያ ክልል የባሌና ጉጂ ዞኖች፤ ድሬዳዋ እና ሀረሪ፤ ከሶማሌ ክልል የፋፈንና ሲቲ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል የዞን 1፣ 3 እና 4፤ እንዲሁም የጌዲዮ፣ የደቡብ ኦሞ እና የሰገን ህዝቦች ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡፡</u>

## እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2021 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በተሰጠው የአየር ጠባይ ትንበያ መሰረት በሚቀጥለው የሴፕቴምበር ወር የመኸር ሰብል አምራች በሆኑትም ሆነ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ የእርጥበት ሁኔታው ጥሩ እንደሚሆንና በተለይም በአንዳንድ የሰሜን ምዕራብ፣ የምዕራብና የመካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ነጎድጓድ እና በረዶ የቀላቀለ ከባድ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ በትንበያው ላይ የተጠቀሱት አብዛኛዉ የኦሮሚያ፡ የአማራ፡ የትግራይ፡ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች፡ የጋምቤላና የቤንሻንጉል-ጉሙዝ ክልሎች እርጥብና በጣም እርጥብ የሆነ እርጥበት እንደሚያገኙ የሚጠበቅ ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ የተሻለ እርጥበት እንደሚኖራቸው ከመጠበቁ ጋር ተያይዞ በቀጣይ ለሚያከናውኑት የግብርና እንቅስቃሴ ገንቢ ሚና እንደሚኖረው ይታመናል። በተለይም ዘግይተዉ ለተዘሩና በእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙትም ሆነ ፍሬ በመሙላት ላይ ላሉት ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች የውኃ አቅርቦት እንዲሁም የሚጠበቀው ቀጣይነት ያለው የእርጥበት ሁኔታ በክረምት ወቅት መጨረሻ በአፈር ውሰጥ በተከማቸው እርጥበት በመታገዝ በደጋማው አካባቢ ለሚዘሩ የጥራጥሬ ሰብሎች አመቺ ሁኔታን እንደሚፈጥር ይጠበቃል። በተጨማሪም ለአርብቶ አደርና ለከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለእፅዋት ልምላሜና ለመጠጥ ውኃ አቅርቦት መሻሻል የጎላ አስተዋፅኦ ያበረክታል፡፡ በሌላም በኩል ከክረምት ዝናብ መጠናከር ጋር ተያይዞ ከባድ ዝናብ በሚጠበቅባቸዉ አካባቢዎች እርጥበቱ ከመጠን በላይ ሊሆን ሰለሚችል በዚህም ምክንያት ውሃ ማሳ ላይ እንዳይተኛ ቦይ በማውጣት፣ የማንጣፈፍና የመከላከል ስራ በመስራት እንዲሁም ከሰብል ጥበቃ አንፃርም ሆነ ከእርጥበት መብዛት ጋር የአረም መከሰትና በየጣልቃው ከሚኖረው ሙቀት ጋር ተዳምሮ ለፀረ ሰብል ተባይ አመቺ ሁኔታን ሊፈጥር ሰለሚችል የሚመለከተው ክፍል የማሳ ጉብኝት በየጊዜው በማድረግ አረምን በወቅቱ በማረም፣ ፀረ-አረምና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን በወቅቱ ከግብርና ባለሙያ በሚያገኙት ምክረ ሀሳብ በመደገፍ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የሚጠበቀው ከባድ ዝናብ በረባዳማ፣ ውሃ ገብና በወንዝ ዳርቻ ባሉ ማሳዎች ላይ ጉዳት ሊያስከትል ስለሚችል በተጠቀሱት አከባቢዎች በሰብሎች፣ በእንስሳትና በንብረት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

## እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2021 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሀው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመጪው ክረምት ወቅት የመጨረሻ የሴፕቴምበር ወር የክረምቱ የተሻላ የእርጥበት ሁኔታ በአንዳንድ የሰሜን ምዕራብ፣ የምዕራብና የመካከለኛዉ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ እንደሚሰተዋል ትንበያው ያመለክታል፡፡ በተጨማሪም የክረምቱ እርጥበት መጠን ከሞላ ጎደል ከመደበኛዉ ጋር ተቀራራቢ በሆነ ጊዜ ከአብዛኛዎቹ የወቅቱ እርጥበት ተጠቃሚ ተፋሰሶዎች ላይ ሊያቆም እንደሚችል ይጠበቃል፡፡ ይህንን ተከትሎ በአብዛኛው ተከዜ፣ አባይ፣ ባሮአኮቦ፣ አዋሽ፣ የላይኛውና የመካከለኛው ኦሞጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ እንዲሁም ገናሌዳዋ ተዋሳኝ ከፍተኛ ቦታዎች ከበጣም ከፍተኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት መጠን ሊያገኙ እንደሚችሉ የትንበያ መረጃዎችን ያመለክታሉ፡፡ በተጨማሪም የታችኛው አዋሽ፣ የላይኛውና የመካከለኛው ዋቢሸበሌ፣ የላይኛው አፋር ዳናክል እና የመካከለኛውና የታችኛው ኦሞጊቤ አነስተኛ የእርጥበት መጠን እንደሚኖራቸው ይጠበቃል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች ላይ የሚዘንበውን ከፍተኛ ዝናብ ተከትሎ የወንዞች ከመጠን በላይ መሙላት ቅፅበታዊ ጎርፍ እንዲሁም የመሬት መንሸራተት በተለይ በላይኛውና መካከለኛው ስምጥሸለቆ፣ በታችኛው አዋሽ፣ አባይ፣ ኦሞጊቤ እንዲሁም በባሮአኮቦ ተፋሰሶች ላይ ሊከሰት ስለሚችል የሚመለከታቸዉ የህብረተሰብ ክፍሎችና አካላት ከወዲሁ አስፈላጊውን ክትትልና ቅድመጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡